# ግርግርና ረብሻ ባሕላችን እንዳይሆን

በሕዝቡ ላይ ያደረው የቅንጅት መንፈስ የዝማሬው አዝማች እንዲህ ነበር። " **ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ**"። ራቁቱን የቆመ ወያኔ ላይ ጣት መቀሰርና እብድ እብድ እያሉ መጮህም ቀላል ነበር። በመሆኑም አዋቂዎችም አፋሞችም ተቀናጅተው እኩል ገነኑበት። ጀበና በእሳት እንዲሙዋሽ ሁሉ ቅንጅትም የደም ግብር ገብቶለት ሊፈተን ቃሊቲ ወረደ። '**እያንጓለለ**' በለጠና ተሰባበሩ አምስት ለአራት በሆነ ብልጫ ተባበሩን አሸነፈው። 'ሰ' ጉድ አደረገቺኝ እያለ የቅንጅት መንፈስ ቃሊቲ ቀረ። ጦሱ ለብርቱዋ ተረፈና ቃሊቲ ጠራት። ቅንጅት የነሺብሬ የደም ግብር ገብቶለትም ከመሰነጣጠቅ አላመለጠም። እርስ በእርሱ ተጠላልፎም "…. እኔ ግንድ ነኝ የሚገነጠለው ቅርንጫፍ ነው። …" በሚሉና "…. የዛፉ ፍሬ በቅርንጫፎቹ ላይ ስለሆነ ተባዝቶ የመብቀልም ዛፍ የመሆንም ተስፋው እኔ ዘንድ ነው። …" በሚሉ ቅርንጫፎች መካከል ግርግርና ረብሻ ሆነ። ግንዱም ላለመገርሰስ ይበጀው ዘንድ በስሮቹ አማካይነት ወያኔ ላይ ተጠመጠመ። እናም በመደራደር ስም ተንደረደረ። እጅ በመዘርጋት ስም ተዘረጋ። በሳሱት ስሮቹ ተብትቦ ወያኔን ይጣለው ወይስ ወያኔ እየቀለበ ለናሙና ያስቀምጠው የምናውቀው የለም።

ተባዝቶ የመብቀል አቅም አለን፣ የመንፈሱ ወራሾችም እኛው ነን ያሉ 'አንድነት' ሆነው እርግጥም የማደግ ምልክት አሳዩ። ግና ሽቅብ ሳይሆን አግድም አደጉና መጠላለፋቸው በዛ። በስተመጨረሻም የስነምግባር እርምጃ ወሰድን በሚሉና በ'**ዝም አንልም**' ተከፍለው የሰላሙ ታጋዮች እርስ በእርሳቸው ጠመንጃ ቀረሽ ረብሻ ይራበሹ ጀመር። አንደኛቸው አድማ መቺ ሌላኛቸው አድማ በታኝ ሆነው በአገር መድረክ ላይ ድርማ ይሰራሉ። ለመሪያቸው ለብርትኳን ከወጡት ሰልፍ እርስ በእርስ ለመናቆር የወጡት በለጠ። ደምቆም ተሰማላቸው። የሚገርመው ብዙዎቹ በዘመነ ማርክሲዝም የሚታረቅና የማይታረቅ ቅራኔን ሲተነትን ከነበረው ትውልድ መሆናቸው ነው። ሊታረቁ ከሚዳዳቸው ተቃቅፈው፣ ሊራራቁ ከማይገባቸው ጋር ተናክሰው ፍትህ ከወያኔ እየለመኑ ጉድ ጉድ ያስብሉናል። የቅንጅት መንፈስ ቢከዳቸው የመበተን መንፈስ አድሮባቸው እርስ በእርስ እየተቆራቆሱ ወያኔን ገላግለን ይላሉ። እነ 'ዝም አንልም' ይህን ያህል አቅም አለን የሚሉ ከሆነ ቃሊቲ በራፍ እየተገኙ ምነው ለመሪያቸው እንዲህ በሆኑ ያሰኛል። ፓርላማ በር ላይ ቆመው መሪያችንን አስራችሁ ዝም የለም ቢሉ እንዴት ባማረባቸው። እንዲያው ይሄ ግርግርና ረብሻ አብሮን አድጎ ይሆን ሊመሩን ያሰቡ መሪ እንደጠፋው መንጋ በየአቅጣጫው የበረገጉብን? ያለበለዚያ እኮ ዘመናት ባለፉ ቁጥር ራሳችንን መልሰን እዛው እናገኘው ዘንድ አይገባንም። መለወጥ ማደግ መቻል አለብን። ከግርግርና ከረብሻ በላይ መሆን መቻል አለብን ብለን ልናምን ይገባናል። ድርጊታችን ማንን ይጎዳል ማንንስ ይጠቅማል? ከማለት ይልቅ የቅርብ የቅርባችን ላይ ቡጢ ማንሳት የብልህ መንገድ አይደለም።

ያኔ ድሮ የመንግስቱ ንዋይ የለውጥ ትግል 'ግርግር' እንደተባለ ቀርቷል። የተማሪዎችም የለውጥ እንቅስቃሴ 'ረብሻ' የሚለውን ስያሜ ተቀብሎ ይኖራል። መስዋዕትነት የከፈሉ ሰዎች እንደዋዛ በመንግስቱ ንዋይ 'ግርግርና' በተማሪዎች 'ረብሻ' ጊዜ የሞቱ ተብለው ሕልፈታቸው በግርግርና ረብሻ ተሰይሞ ቀረ። ግርግርና ረብሻ ለእንቅስቃሴአቸው መገለጫው ከሆነ ሁዋላ ስማቸውስ እንዴት ይወሳል? ያው በግርግር የሞቱ በረብሻ ያለቁ ይባሉ ዘንድ ግድ ይላል። እንደ እውነቱ ከሆነና አሁን እውነቶች መውጣት ሲጀምሩ እንደምናየው እኮ የተማሪው ነገር በእውነትም ረብሻ ነበር። ከንቱ የፈሰሰው የሀገር ወዳድ ተማሪዎችን የደም ጎርፍ ያንዠቀዠቁ መንገዳቸውን የሚያውቁ መሰሪዎች በጣም ጥቂት ነበሩ።

በአንድ ሰው የእድሜ ዘመን ጃንሆይ አጠፉ ተባሉ እናም ጠፉ፣ የዘመነ አብዮት ድርጅቶች አንደኛቸው በሌላኛው ሲጠፋፉ ከርመው በስተመጨረሻ ሰደድ ሁሉን አጥፍቶ ከነመሪው ስደት ገቡ። ንጉሱን አጠፉ ብሎ ያጠፋቸው ደርግም ጠፋ። የትግራይ ሕዝብ ተጨቆነ ብሎ የትግራይ 'ጨቋኞችን' በማርክሳዊ በትር እያጠፋ የኖረው ወያኔም ደርግን አጠፋሁ አለ። ወር ተራው የደረሰው ወያኔም የሚያጠፋውን ገና ባንለይም ለመጥፋት ግን መሰናዶውን አጠናቅቆአል። ስለዚህ የሹም ሽር ባህላችን በተራ ሳይሆን አጥፍቶ በመጥፋት ነው ማለት ነው። እንዲያ እርስ በእርስ ስንጣፋ ሀገሪቱ ሆና የማታውቀውን የውጭ አገር ሰዎች የሚመዘብሯት አገሬው በግርድናና ባሽከርነት የእለት ጉርሱን የሚያገኝባት አገር እየሆነች ነው። በጦርነት ሳይሆን በመልካም ፈቃድ ተሸናፊ ሆነን በርካቶቻችን ባርነትን እየተቀበልን ነው። ፖለቲከኞቻችን በግርግርና በረብሻ በመራኮት፣ ገሚሶቻችን በስደት፣ ገዢዎቻችን ደግሞ አገር በታላቅ ቅናሽ በመሸጥ።

እንደ ኢትዮጵያዊ አንድ የሚያደርገን ትንሹን ትልቁን የሚያቆራኝ፣ የተማረውንና ያልተማረውን የሚያስተሳስረው ባሕሉ፣ ልምዱና ወጉ ነው። ታድያ በዚህ ቅንፍ ውስጥ ነው ጉድፋችንን እናወጣ ዘንድ የሚገባን። ፍቅር አለን መተሳሰብ አለን እንላለን፣ አገራችን አደረገችልንም አበሳችንን አስቆጠረችን አጥብቀን እንወዳታለን። በዚህ ሁላችንም አንድ ነን። ምቀኝነትና ክፋትም፣ እልህና ቂመኛነትም የባህሪያችን መገለጫዎች ናቸው። ተማርን አልተማርን አገር ቤት ኖርን በውጭ አገር ይቺ ጠባይ የትም ትከተለናለች። ስለዚህም ነው ብዙ የሚጠበቅባቸው ምሁሮችና የኔ ቢጤዎቹም እንደ አቅማችን ተመሳሳይ ባህሪይ የምንላበሰው። የሚገርመው በ 1940 ዎቹ የነበረው ሁኔታና ዘንድሮ የምናየው የማኅበረሰባችን የግንኙነት መርህ አንዳች ለውጥ ያለማሳየቱ ነው። በዚያን ዘመን እኛ አብረን መስራትና ማሰራት እንደማንችል አበሾቹ፣ እንግሊዞቹ፣ ግብጾቹና ሱዳኖቹ በግልጽ ይናገሩት ነበር። (አንዳንድ በአማርኛ በኛው ሰዎች የተጻፉ መጻህፍቶችን ማገላበጥ ይቻላል) ዘንድሮም እንደዚያው ነው። ማን ያሰራሃ/ሻል? የሚለው ጉዳይና ያለው ውዝግብ እንዳለ ነው።

መነጋገር የማንችል፣ መደማመጥ የማይሆንልን እንበዛለን። ስለዚህ አንዳንዴ በፍቅር አብረን ልንዝናና ወጥተን በዱላ ተፈነካክተን እንመለሳለን። ለለውጥ ታገልን የምንልም ተማርን ብለን የምንመጻደቅ ሰዎችም እንዲሁ ብዙ ጊዜ ሀሳባችንን ለመለዋወጥ እንኳ ትዕግስት የለንም። በዱላ ባንፈነካከትም በብዕር (ስድብና ዝርጠጣ) እንጫረሳለን። ለጉልበተኛ አድረን የጠላነውን እናስወጋለን። የሀሳብ ልዩነትን ማቻቻል ወይም መቀበል የሚከብደን ብዙ ነን። ምክንያቱም ላለፈው የቆየ ቂም ለወደፊቱ ደግሞ የግል ጥቅም ሰቅዞ ስለሚይዘን የሚበጀውን ፈቅደን ወደፊት መራመድ አይቻለንም። ስኅተትን መቀበልና ይቅርታ መጠየቅም ለብዙዎቻችን የውርደት እኩሌታ ይሆንብናል። ስለዚህ ስማችን በወቀሳ ከሚነሳ ግርግር ብንፈጥር ረብሻ ብናስነሳ እንወዳለን።

ጀግና ማለት የሚታገስ ነው፣ ጀግና ማለት አስቦ የሚከውን ማለት ነው። ጀግና የምንላት መተባበርም ማስተባበርም የምትችልን ነው። ጀግና ማለት በእርስዋ መስዋዕትነት የሌሎችን ሕይወት ማቆየት የምትችልና ለድል የምታበቃ ማለት ነው። ጀግንነት የምንለው በትንሽ መስዋዕነት ትልቅ ድልን የመጎናፀፍን ጥበብ ማወቅን ነው። ጀግንነት በእኔ መንገድ ካልሄዳችሁ ገደል ግቡ ከሆነ፣ ተራ በተራ ወደ ገደል ሲወራወሩ እንደነበሩት አጥፍተው የጠፉ የዘመነ ሶሻሊዝም የፖለቲካ ድርጅቶች የዛሬዎቹም ለመጥፋት መንደርደራቸው መሆኑን ያለማወቅ ግብዝነት ነው።

ዓላማችን አገር እያጠፋ ያለውን ወያኔን አሽንፎ አገራዊ ክብራችንን ለሚያስመልስልን በነፃነት እንኖር ዘንድ የሚያመቻችልንን መንግስት መመስረት ከሆነ ተቃዋሚዎችን አንድ የሚያደርግ ጉዳይ አለ። በወያኔ አገዛዝ ምትክ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት ዓላማችን ከሆነ አንድ የሚያደርጉን መሰረታዊ ጉዳዮች አሉ። በትረ ስልጣን የሚያዘው ዲሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ በምርጫ ብቻ ነው ብለን የምናምን ከሆነ አንድ የሚያደርገን ነገር አለ ማለት ነው። የግለሰብ መብትን መከበር የምንደግፍ ከሆነና በኢትዮጵያ ሉአላዊነት ላይ አወዛጋቢ አቋም ከሌለን አንድ የሚያደርጉን በርካታ ጉዳዮች አሉ ማለት ነው። ሌሎችም አገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አንድነታችንና ልዩነታችን አበጥረን ካወጣን መልካም ጅምር ይሆነናል። በዚህ ጉዳይ ላይ በቂ እውቀት መያዝ ብንችል አስመሳዩና ስልጣን በአቋራጭ መንጠቅ የሚፈልገው ተለይቶ ቢታወቅ፣ እንደ ድርጅት እስከ አሁን ያከናወናቸው ጉዳዮች ቢገመገሙ ለተጠያቂነት ያለው ቅድመ ዝግጅትም ይታወቃል። የከረመ ቂማቸውን ለመወጣት፣ የግል ፍላጎታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ፣ ዝናና ክብር ፍለጋ፣ ጥቅም ፍለጋ፣ ለሌብነትም ጭምር የሚመጡትን መለየትም አዳጋች አይሆንም።

ጉዳዩ ኢትዮጵያን እንደ አገር በማቆየትና ጭራሹን በመፈራረስ መካከል መሆኑን መረዳት የሚገባን ጊዜው ነው። ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንደ ውሃ ባለሀብትነትዋ፣ እንደ ታላቅ የእርሻ መሬት ባለቤትነትዋ ገና የሚጠብቃት ፍዳ መኖሩን ያለመዘንጋት አስፈላጊ ነው። ኢትዮጵያ ከሌለች የምንሻው ስልጣን አይኖርም። ባንዲራም ያለ ሀገር ባለ ቀለም ጨርቅ ይሆናል። ፓርቲም ያለ ሀገር የመረዳጃ ማኅበር መሆን እንኳ አይችልም። መለስ ዜናዊ ደግሞ ቃል የገባልንን ባንዲራችንን እጃችን ላይ ጨርቅ የማድረግ ተልዕኮውን በሚገባ እያከናወነ ነው።

አሁን በያዝነው ጎዳና ብንገሰግስ ከረብሻና ከግርግር አናልፍምና ለመቃወም ስንል ብቻ አንቃወም ከለመደብን ቅንጅት ቅንጅትን እንደሚቃወመው ራሳችንንም ስንቃወም እንኖራለን። እስቲ ተቃዋሚ ነን ከምንል ደጋፊ ነን እንበልና በጉልበት ጊዜና እውቀታችን ለተቃውሞ ማድረግ ትተን ለድጋፍ እንነሳ። ባርነትን ትተን ነፃነትን፣ ገዳዮችን ትተን አዳኞችን፣ ወሬኞችን ትተን ሰራተኞችን፣ ረሀብን ትተን ጠግቦ ማደርን እንደግፍ። የተሸነፍንበትን ትተን ያሸነፍንበትን ከፍ እናድርግ!! ያጠፋትን ስንወቅስና ስንከስ አማርኛችንን ከምንራቀቅበት፣ በሆይ ሆይ ደግፈናቸው በዋይ ዋይ ማውረድ ከምንሞክር በቅድሚያ መመርመር እንቻል። ለመመርመር ደግሞ የእውቀት ስንቅ ያስፈልጋልና ስንቃችንን ሸክፈን ከዚያ በሁዋላ የምንደግፋቸው ላይ ትኩረት እናድርግ ። ስለ ሀገር የሚተጉት በሙሉ ችግር ላይ ናቸው። ሁሉም ለምነው አዳሪ ናቸው። ራድዮኖች መረጃ ያቀብላሉ ግን በሚያታክትና ቅስም በሚሰብር ልመና ነው ስራቸውን የሚሰሩት። በርካቶቹ በግለሰብም ይሁን በድርጅት መልክ ያሉት እንደዚያ ናቸው። አሰፍስፈን የምንጠብቀው ሲዳከሙ ልንወቅሳቸው ሲሳቱ ልንፈርድባቸው ነው። ነገር ግን እሮሮና ፀፀት ወደሁዋላ እንጂ ወደፊት አይወስደንም። እስቲ የምንቃወማቸውን ለማሸነፍ የምንደግፋቸውን እንርዳ፣ ዳር ቆመን ከመተቸት ገብተን እንሞክረው። ያልዘራነውን ልናጭድ አይቻለንምና ነብሳችንን ሸሽገን በሌላው ነብስ አንማማል። ገንዘባችንን ቀርቅረን ውጤት አምጡ አንበል።

ይህ በውስጣችን የሥነልቡና ለውጥ ሊያመጣ ይችል ይሆናል። ቀና አስተሳሰብና ደስተኛነትንም ሊሰጠን ይችላል። ተቀጥቅጦና ተነቅፎ ያደገ ትውልድ ውስጥ ከማድነቅ ይልቅ ማንኳሰስን ሊመርጥ አእምሮው ተለማምዶአል። ስለዚህ ከመደገፍ ይልቅ መቃወም ይመርጣል። አዳራሾች ክስና ሙግት ያለበት ይደምቃሉ። ፀብ ያለበት መፈናፈኛ የለም። መድረክ የሚጠባቸው ከሳሾች የነገር ወንጭፋቸውን ይዘው ብቅ ይላሉ። እስቲ ከመወንጨፋችሁ በፊት የምትደግፉትንና ለዚያም ያደረጋችሁትን አስተዋጽኦ ተናገሩና ከዚያ መድረኩ ይሰጣችሁ ቢባሉ በርካቶች ትንፍሽ እንደማይሉ መገመት አይከብድም። ስለዚህ አሰላለፋችንን መቀየር ይኖርብናል ብዬ አስባለሁ። በመቃወም ሳይሆን በመደጋገፍ፣ በመተሳሰብና በጥንካሬያችን ላይ በመገንባት ነው ካሰብንበት የምንደርሰው። መነጋገር ሳንችል አንደራጅ። ተጓትተን ለመውደቅ ስንልም አንተባበር። በቅጡ ሳንደራጅም አንደራደር። በዚያ መንገድ ከቀጠልን ግርግርና ረብሻ ባሕላችን ሆኖ ሊቀር ይችላል።

ከግርግርና ከረብሻ እንድንላቀቅ እግዚአብሄር የጥበብ ብርሃን ያብራልን።

ዳኛቸው ቢያድግልኝ
biyadegelgne@hotmail.com